# ዋሽንግተን ዩዝ ዴቨሎፐመንት ለትርፍ ያልተቋቋመ የበጎ አድራጎት ፈንድ
# የፕሮፖዛል ጥያቄ (RFP)

## መንደርደሪያ/መግቢያ

ፐየዋሽንግተን ግዛት የንግድ መምሪያ **በዋሽንግተን ዩዝ ዴቨሎፐመንት ለትርፍ ያልተቋቋመ የበጎ አድራጎት ፈንድ** አማካኝነት የእርዳታ አሰጣጥ አሸናፊነት ሂደትን ለመተግበር ከስኩልስ አውት ዋሽንግተን (SOWA) ጋር አጋርነት ፈጥሮ እየሰራ ነው።

SOWA በግዛቱ ውስጥ በጠቅላላው በ COVID-19 ወረርሽኝ የተነሳ በእጅጉ ጉዳት ላጋጠማቸውና ከትምህርት ፍትህ ለራቁ ወጣቶች አገልግሎት ለሚሰጡ የወጣት ልማት ፕሮግራሞች/ድርጅቶች የሚደረገውን የ$9.3 ሚሊዮን ኢንቨስትመንት ያስተዳድራል።

የCOVID-19 ወረርሽኝ መስፋፋት፣ የተራዘመ የትምህርት ቤቶች መዘጋት፣ እና ማህበራዊ ርቀትን የመጠበቅ ገደብ በመላው ዋሽንግተን የሚገኙ ህጻናትና ወጣቶችን እኩልነቶች ማጣትና ችግር ስር እንዲሰዱ አድርገዋል። የወጣት ልማት ፕሮግራሞች/ ድርጅቶች ለወጣቶችና ከወጣቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ላላቸው ቤተሰቦች - የአስቸኳይ ጊዜ የህጻናት እንክብካቤን፣ የማህበራዊ - ስነ ልቡናዊ ድጋፎችን፣ የትምህርት ስልጠናን፣ የቨርቹዋል ፕሮግራምን እና የመሰረታዊ ፍላጎቶች ድጋፎችን ጨምሮ ምላሽ ሰጪ ድጋፎችን ለማቅረብ አገልግሎቶቻቸውን አዘጋጅተዋል።

የበጎ አድራጎት ፈንዱ የታጣው ገቢና የ COVID-19 የደህንነት እርምጃዎችን ለማሟላት ከተከፈሉ ከፍተኛ ወጪዎች ጋር በጥምረት ብዙ ድርጅቶችን ፕሮግራሞቻቸውን ወይም የስራ ቦታዎቻቸውን ለመዝጋት ስጋት ያጋለጧቸው መሆኑን በመገንዘብ በ COVID-19 ምክንያት ለተፈጠሩ የገንዘብና የፕሮግራም ተግዳሮቶች መፍትሄ ይሰጣል።

## የRFP ጥቅል ሀሳብ

ይህን RFP ከመስጫ ጀምሮ የገንዘብ ድጋፍ አሸናፊነቶችን የማሰራጫ የጊዜ ሰሌዳው አጭር ነው። ፕሮፖዛሎች እስከ ጥቅምት 6፣ 2020 ዓ.ም ድረስ በኦንላይን መቅረብ አለባቸው። ማመልከቻዎቹ ከቀረቡ በኋላ እስከ ታህሳስ 15፣ 2020 ዓ.ም ድረስ ፕሮፖዛሎቹ ይመረመራሉ፣ የገንዘብ ድጋፎቹ ይሰጣሉ እንዲሁም ጠቅላላ ሂደቱ ይጠናቀቃል። (የበለጠ የተሟላ የጊዜ ሰሌዳ ከዚህ በታች ቀርቧል።)

የበጎ አድራጎት ፈንድ እርዳታዎቹ የሚሰጡት መሰረታቸውን በዋሽግተን ግዛት ውስጥ ላደረጉ ወይም ለወጣቶች አገልግሎት እየሰጡ ላሉ ድርጅቶች ብቻ ነው።

በመላው ግዛት ውስጥ እኩልነትን ማስቀጠል እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ወጣቶችንና በ COVID-ተጽእኖ የተፈጠረባቸው ፕሮግራሞች/ድርጅቶችን ማሳተፍ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ RFP ቀላል፣ አነስተኛ መሰናክል የሚያጋጥምበት የኦንላይን ማመልከቻ ያቀርባል።

አመልካቾች ሙሉ የወጣት ልማት ድርጅታቸውን ወክለው ወይም የሚያንቀሳቅሱትን ልዩ የወጣት ልማት ፕሮግራም ወክለው ማመልከቻዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ። ከአንድ ድርጅት ተቀባይነት የሚኖረው አንድ ብቻ ማመልከቻ ነው። የዚህ ልዩ ሁኔታ የሚፈቀደው ለሌላ ፕሮግራም/ድርጅት የፊስካል ወኪል ሆኖ ለሚያገለግል የወጣት ልማት ደርጅት ነው። በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት እያንዳንዳቸው ማመልከቻ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

ከመንግስት ወይም የግል ምንጮች ሌላ የ COVID-19 የበጎ አድራጎት የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ፕሮግራሞች/ ድርጅቶች ለበጎ አድራጎት የገንዘብ ድጋፉ ለማመልከት ብቁ ናቸው።

ማመልከቻው ስለ ፕሮግራሞቹ/ድርጅቶቹ የተመለከቱ አጭር ማብራሪያዎችን፣ የወጣት ተሳታፊዎች አሀዞችን፣ የፕሮግራሞቹ/ድርጅቶቹ ብቁነት ማረጋገጫን፣ ለእነዚህ ሶስት ዋና ዋና ቅደም የሚቀርቡ አጭር ማብራሪያና ምላሾችን እና የበጀት መረጃ ማጠቃለያን ማቅረብን ይጠይቃል። ምንም የበጀት ቅጾች አይጠየቁም።

ምላሽ ሰጪዎች በእነዚህ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ ብቁነትን ለማረጋገጥ በማመልከቻው ላይ በተቀመጡ ሳጥኖች ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ፡

- ☐ በ501 (c)(3) ለትርፍ ያልተቋቋመ ወይም በ501 (c)(3) የገንዘብ ስፖንሰር የሚደረግለት ድርጅት/ፕሮግራም
- ☐ ከ COVID-19 ወረርሽኝ መከሰት በፊት ለህጻናትና እድሜያቸው ከ5-24 ዐመት ለሆኑ ወጣቶች የወጣት ልማት አገልግሎቶች የሚያቀርብ ፕሮግራም/ድርጅት
- ☐ በቅርቡ ለወጣቶች በአካል፣ በቨርቹዋል የቀረቡ ወይም ለማቅረብ የታቀዱ አገልግሎቶች፣ ወይም ከመጋቢት እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ድረስ የሚቀርቡ ቀጥተኛ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ድጋፎች።
- ☐ በ COVID-19 መከሰት የተነሳ ድርጅቱን/ፕሮግራሙን ያጋጠመ ኔጋቲቭ/አሉታዊ የገንዘብ ተጽእኖ።

የብቁነት መስፈርቱን የሚያሟሉ ምላሽ ሰጪዎች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ለሚዳስሱት ሶስቱ ዋና ዋና ቅደም ተከተሎች አጭር ማብራሪያ እና ምላሾች ማቅረብ፣ እና የተጠቃለለ የ2019 ዓ.ም እና (የታቀደ) የ2020 ዓ.ም የገቢና ወጪ መረጃ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡

1. ቅድሚያ በሚሰጣቸው ከትምህርት ፍትህ በራቁ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት የሚያገኙ ወጣቶች
2. የፕሮግራሞች/ድርጅቶች ሰራተኞችና አመራር
3. የCOVID-19 ወረርሽኝ ተጽዕኖ

## የቴክኒክ ድጋፍ

RFPው ወደ አማርኛ፣ አረብኛ፣ የቻይኒስ ማንዳሪን፣ ኮርያኛ፣ ማርሻሊስ፣ ራሻኛ፣ የሳሞአ፣ ሱማሊኛ፣ ስፓኒሽ ታጋሎግ፣ ቶንጋ፣ ዩክሬንኛ እና ቬትናምኛ ቋንቋዎች ይተረጎማል። የተተረጎመውን RFP እንዴት ማግኘት እንደሚቻል የተመለከተ መረጃ እዚህ ላይ ማግኘት ይቻላል። የኦንላይን ማመልከቻዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅረብ አለባቸው።

Commerce የ RFP መስፈርቶቹን መረዳትን እና የእርዳታ የጽሁፍ ድጋፍ መስጠትን ጨምሮ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻውን በመሙላት ላይ ድጋፍ ለማግኘት ከተለያዩ የቴክኒክ ድጋፍ አቅራቢዎች ጋር ግንኙነት አድርጓል። የቴክኒክ ድጋፉ በመላው ግዛቱ በእንግሊዝኛና በተለያዩ ሌሎች በድረርጅቶች በሚቀርቡ ሌሎች ቋንቋዎች ይቀርባል። አመልኪቾች የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት በቀጥታ ከቴክኒክ ድጋፍ አቅራቢዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ አለባቸው። የግንኙነት መረጃና የቋንቋ ድጋፎችን የተሟላ ዝርዝር ከ SOWA's የበጎ አድራጎት ፈንድ ድረ ገጽላይ ላይ ማግኘት ይቻላል።.

RFP ን በተመለከተ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበት የመረጃ ክፍለ ጊዜ በታህሳስ 24፣ 2020 ዓ.ም በ4:00 ሰዐት እና በመስከረም 29፣ 2020 ዓ.ም በ6:30 ሰዐት በZoom ስብሰባዎች ይካሄዳል። የ SOWA's የበጎ አድራጎት ፈንድ ድረ ገጽ በመጎብኘት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘትና ለመመዝገብ ይችላሉ።

RFPን የተመለከተ FAQ ከ SOWA's የበጎ አድራጎት ፈንድ ድረ ገጽላይ ማግኘት ይቻላል። በመረጃ መስጫ ክፍለ ጊዜው ላይ ወይም በ youthdevrelief@schoolsoutwashington.org የሚቀርቡ ሁሉም አዲስ ጥያቄዎች ይጨናሉ። የFAQ ማሻሻያዎች RFPው ክፍት ሆኖ በሚቆይባቸው ሁለት ሳምንታት ውስጥ ቢያንስ ሶስት ጊዜያት ይሰጣሉ። ተጨማሪ መረጃ ከዚህ በታች በ RFP የጊዜ ሰሌዳ ስር ተካቷል።

## የፕሮፖዛል ግምገማ/ምርመራ ሂደት

SOWA ትኩረቱን ጠንካራ ክልላዊ እና የ BIPOC (ጥቁር፣ የአካባቢ ተወላጅ፣ የተለያየ የቆዳ ቀለም ያላቸው ሰዎች) ተወካዮችን መቅጠርን አድርጎ ወደ 150 ያክል የፕሮፖዛል ገምጋሚዎችን ለማሳተፍ መጠነ ሰፊ፣ ግዛት አቀፍ ስምሪት እያካሄደ ነው። አነስተኛ የገምጋሚዎች ቡድን በመሪ ገምጋሚነት ከሚያገለግሉ ከዋና ዋና አጋሮች ጋር አንድ ላይ ሆኖ ይሰራል። የገምጋሚ ቡድኖች ከየክልሎቻቸው የቀረቡ ፕሮፖዛሎችን ይገመግማሉ። በፍቃደኝነት የሚያገለግሉ ግዛት አቀፍ ገምጋሚዎች ለሁሉም ክልሎች ቡድኖች ይከፋፈላሉ።

ሁሉም ገምጋሚዎች የጥቅም ግጭቶችን ይፋ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ። የግምገማ ቡድን ተግባሮች የትኛውም ገምጋሚዎች በሰራተኝነት፣ የቦርድ አባልነት ወይም አማካሪነት ከሚያገለግሉባቸው ፕሮግራሞች/ድርጅቶች የቀረቡ ፕሮፖዛሎችን አለመገምገማቸውን ያረጋግጣሉ። ለገምጋሚዎች የፕሮፖዛል ግምገማ ከመጀመራቸው በፊት የፀረ መድልዎ ስልጠና ይሰጣቸዋል። በመላው ግዛት የሚሰማሩ ገምጋሚዎች ተመሳሳይ የውጤት አሰጣጥ መስፈርቶች ይጠቀማሉ።

ስኩልስ አውት ዋሽንግተን/School's Out Washington የግምገማ ቡድኖችን በማመቻቸት ረገድ መሪ ገምጋሚዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ማገዝን ጨምሮ የግምገማ ሂደቱን ይመራል። አንዴ የግምገማ ቡድኖች ግምገማውን እና የውጤት አሰጣጥ ሂደቱን ካጠናቀቁ በኋላ SOWA የሁሉንም ቡድኖች የውጤት አሰጣጥ ይገመግማል።

## የግምገማ ቡድኖች ጂኦግራፊያዊ ስምሪት እና የእርዳታ አሸናፊነት አሰጣጦች

ከዚህ በታች የተመለከተው ካርታ በግዛቱ ውስጥ የሚገኙ ከስድስት አስተዳደራዊ ክልሎች የዋሽግተን የህጻናት፣ ወጣቶችና ቤተሰቦች መምሪያ (DCYF's) ጋር በህብረት የሚሰሩ ስድስት ክልሎችን ይዘረዝራል። SOWA የ DCYFን ክልሎች የፕሮፖዛል ገምጋሚ ቡድኖችን ለመመደብ እና የእርዳታ አሸናፊነት ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ግዛቱን በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እንደ መክፈያ ዘዴ ይጠቀምበታል።

የእርዳታ ገንዘቡን በመላ ግዛቱ የማከፋፈል ግቦች ከእነዚህ ክልሎች ሁለት ልዩ ዋና ዋና የዳታ ነጥቦች ማለትም፡ እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በታች የሆኑ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶች፤ እና እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በታች የሆኑ BIPOC ወጣቶች ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ከዚህ በታች በተመለከተው ካርታ ላይ የመቶኛ ምደባው በእያንዳንዱ ክልሎች በሚኖሩ የዋሽግተን እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በታች በሆኑ በድህነት ውስጥ በሚኖሩ ወጣቶች መቶኛ፣ እና የዋሽግተን እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በታች በሆኑ BIPOC ወጣቶች መቶኛ ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህ ዳታዎች የእርዳታ ገንዘቡን ለክልሎች የማከፋፈል ግቦችን ለመወሰን በእኩል ደረጃ ይመዘናሉ። እነዚህ ለጂኦግራፊያዊ ክፍፍል ግቦች ሲሆኑ እነዚህን ማሳካቱ ከእያነንዳንዱ ክልል በሚቀርቡ ብቁና ከፍተኛ ውጤት በሚያገኙ ፕሮፖዛሎች ብዛት ላይ የተመሰረተ ነው።




## የፕሮፖዛል ምርመራ/ግምገማ መስፈርት

ሶስቱ ዋና ዋነ የማመልከቻ ቅደም ተከተሎች (ከላይ በፕሮፖዛል ጠቅላላ ሀሳብ ስር የተገለጹት) የፕሮፖዛል ፍምገማ መዋቅርን ይሰጣሉ።

የውጤት መስጫ መስፈርቱን በመጠቀም ገምጋሚዎች ፕሮግራሞች/ድርጅቶች እንዴት እና በምን ያክል መጠን የሚከተሉትን እንደሚያሟሉ ይገመግማሉ፡

| | |
|---|---|
| 1. ቅድሚያ በሚሰጣቸው፣ ከትምህርት ፍትህ የራቁ ወጣት የማህበረሰብ አባላትን ማሳተፍ | የጠቅላላ ውጤት 50% |
| 2. እነዚህን ቅድሚያ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ አባላት በፕሮግራሞች/ድርጅቶች ሰራተኝነትና አመራር ውስጥ ማሳተፍን ማሳየት | የጠቅላላ ውጤት 20% |
| 3. በ COVID-19 የተነሳ ያጋጠመ የገንዘብ እና የፕሮግራም ተጽእኖ/ጉዳት | የጠቅላላ ውጤት 30% |

ገምጋሚዎች የፕሮፖዛል ግምገማቸውን አጠናቀው የመጨረሻ የውጤት መለኪዎቻቸውን ካቀረቡ በኋላ SOWA የሁሉንም ቡድኖች የውጤት አሰጣጦች ይገመግማል።

የግምገማ ቡድኖች ከሚሰጧቸው ምክረ ሀሳቦች በተጨማሪ SOWA በተጨማሪም የመጨረሻ አሸናፊዎችን እና የመጨረሻ የእርዳታ መጠኖችን ውሳኔ ሀሳብ ለ Commerce በሚያቀርብበት ወቅት በመላው ግዛት ቅድሚያ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ውክልናን እና እኩል ጂኦግራፊያዊ ክፍፍልን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

## የእርዳታ አሸናፊነት አሰጣጥ

እርዳታዎቹ በ COVID-19 የተነሳ በእጅጉ ተጽእኖ ለተፈጠረባቸውና ከትምህርት ፍትህ ለራቁ ወጣት የህብረተሰብ አባላት አገልግሎት በሚሰጡት ላይ አጽንኦት በመስጠት በግዛቱ በሁሉም ክልሎች ለሚገኙ የወጣቶች ልማት ፕሮግራሞች/ድርጅቶች ይሰጣሉ።

የእርዳታ መጠኖቹ ከ$10,000 እስከ $50,000 ድረስ ይለያያሉ። ከ $10,000 ያነሰ እና ከ $50,000 የበለጠ እርዳታ የለም።

የእያንዳንዱ አሸናፊ የእርዳታ መጠን ውሳኔዎች በአሸናፊው የ2019 ዓ.ም ወጪዎች መቶኛ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። የእርዳታውን መጠን የሚወስነው መቶኛ በግምገማው ሂደት ወቅት በፕሮፖዛሎች መረጃ ሰር በሚካተት የፋይናንስ መረጃ እና በቀረቡ ፕሮፖዛሎች ብዛት ላይ ተመስርቶ ይወሰናል። አነስተኛ ፕሮግራሞች/ድርጅቶች ከትላልቅ ፕሮግራሞች/ድርጅቶች ይልቅ ከ2019 ዓ.ም ጠቅላላ ወጪያቸው መቶኛ የበለጠ የእርዳታ ገንዘብ ይሰጣቸዋል።

በእርዳታ ፈንዱ አማካኝነት እርዳታዎችን የሚያገኙ ፕሮግራሞች/ድርጅቶች የእርዳታ ተጠቃሚዎችተደርገው ይቆጠራሉ። እርዳታዎቹን ከተቀበሉ በኋላ ተጠቃሚዎች የገንዘብ ድጋፉን ዝውውር ለማመቻቸት፣ የገንዘብ ድጋፉን መቀበላቸውን ለማረጋገጥ እና ድርጅታዊ ታሪኮቻቸውን ለመሙላት በ Elevate Washingtonላይ ቅጾችን እንዲሞሉ ይጠየቃሉ።.

የድጋፍ እርዳታዎቹ ያልተገደቡ የገንዘብ ድጋፎች ናቸው። ምንም ሪፖርት ማቅረብን የሚጠይቁ መስፈርቶች የሉም። የእርዳታ ተጠቃሚዎች እንዴት ወይም መቼ የእርዳታ ገንዘቡን እንደከፈሉት በተመለከተ የትኛውንም የሰነድ ማስረጃ እንዲያቀርቡ አይጠየቁም።

## የጊዜ ሰሌዳ

| | |
|---|---|
| መስከረም 22, 2020 | RFP ይሰጣል |
| መስከረም 23, 2020 | እስከ በ9/24/20 ምሳ ሰዐት ድረስ መልሳቸው ለመለጠፍ፣ ለ FAQ ጥያቄዎች እስከ ምሳ ሰዐት ድረስ ይቀርባሉ |
| መስከረም 24, 2020 | FAQ እስከ ምሳ ሰዐት ድረስ ወቅታዊ ማሻሻ ይደረግበታል።<br>የRFP የመረጃ ክፍለ ጊዜ በ4:00 ሰዐት። ፍላጎት ካሉዎ፣ እባክዎ እዚህ ላይ ይመዝገቡ። |
| መስከረም 28, 2020 | እስከ በ9/29/20 ምሳ ሰዐት ድረስ መልሳቸው ለመለጠፍ፣ ለ FAQ ጥያቄዎች እስከ ምሳ ሰዐት ድረስ ይቀርባሉ |
| መስከረም 29, 2020 | FAQ እስከ ምሳ ሰዐት ድረስ ማሻሻ ይደረግበታል።<br>የRFP የመረጃ ክፍለ ጊዜ በ6:30 ሰዐት። ፍላጎት ካሉዎ፣ እባክዎ እዚህ ላይ ይመዝገቡ። |

| | |
|---|---|
| ጥቅምት 1, 2020 | እስከ በ10/2/20 ድረስ መልሳቸው ለመለጠፍ፣ ጥያቄዎች ለ FAQ እስከ ምሳ ሰዐት ድረስ ይቀርባሉ |
| ጥቅምት 2, 2020 | FAQ እስከ ምሳ ሰዐት ድረስ ማሻሻ ይደረግበታል። |
| ጥቅምት 6, 2020 | RFP ይረከባል |

# የፕሮፖዛል ጥያቄዎች

በእርዳታ ፈንዱ አማካኝነት ለሚሰጡ እርዳታዎች አሸናፊነት ማመልከቻ መሞላት ያለባቸው ጥያቄዎችና መረጃዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ፕሮግራምዎ/ድርጅትዎ ለማመልከቻው የሚሰጣቸው ምላሾች በኦንላይን በ https://youthdevrelief.schoolsoutwashington.org/ላይ መረከብ አለባቸው። እባክዎ ማመልከቻውን መሙላት ከመጀመርዎ በፊረት RFPው ላይ የተገለጸውን መስፈርት ለማሟላት ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

አንዴ የኦንላይን የማመልከቻ ሂደቱን ከጀመሩ በኋላ ወደፊት እየቀጠሉ ሲሄዱ ስራዎን ሴቭ ማድረግ ላይችሉ ይችላሉ። ማመልከቻውን በአንድ ጊዜ መሙላት አለብዎ። በመጀመሪያ በኦንላይን ማመልከቻው ቴምፕሌት ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች መርምረው መልስ ቢሰጡ ከዚያም ጥያቄዎችዎን ለማስገባት ወደ ኦንላይን ማመልከቻ ቅጾቹ ላይ ኮፒ ቢያደርጉ ይመከራል።

የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻውን በመሙላት ላይ የ RFPውን መስፈርቶች መረዳትን እና የእርዳታ አጻጻፍ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ የቴክኒክ ድጋፍ የሚያቀርቡ አቅራቢዎችን ዝርዝር ለማግኘት የ SOWA የእርዳታ ፈንድ ድረገጽን ይመልከቱ። የቴክኒክ ድጋፉ በግዛቱ በሞላ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እና በድርጅቶች በሚቀርቡ በተለያዩ ሌሎች ቋንቋዎች ይቀርባል።

የኦንላይን ማመልከቻዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መረከብ አለባቸው።

## የፕሮግራም/ድርጅት መረጃ

- የማመለክተው የሚከተለውን ወክዬ ነው:
  - ◻ ድርጅት
  - ◻ ፕሮግራም

- ድርጅታችን ለትርፍ ባልተቋቋመ ድርጅት የገንዘብ ስፖንሰር ይደረግለታል:
  - ◻ አዎ
  - ◻ አይ

  *መልስዎ አዎ ከሆነ፣ በዚህ ማመልከቻ መጨረሻ ላይ ከስፖንሰር አድራጊ ድርጅቱ የተሰጠ የገንዘብ ስፖንሰር ግንኙነቱን የሚያረጋግጥ የተፈረመ ደብዳቤ መጫን ይጠበቅብዎታል።

- ይህ ማመልከቻ በሚያተኩርበት ድርጅት ወይም ፕሮግራም አገልግሎት የሚያገኙ ሁሉንም ካውንቲዎች ይምረጡ፡:

- የድርጅቱ ህጋዊ ስም:

- የገንዘብ ስፖንሰር አድራጊ ድርጅቱን ስም ይግለጹ፤ ተፈጻሚ ከሆነ:

- የቀጣሪ መለያ/መታወቂያ ቁጥር (EIN):
  ማስታወሻ: ፕሮግራሙ/ድርጅቱ የገንዘብ ስፖንሰር አድራጊ ካለው እባክዎ የገንዘብ ስፖንሰር አድራጊውን EIN ያስገቡ።

- የተዋሀደ የስራ መለያ/መታወቂያ (UBI) ቁጥር:

- ዋና የስራ አድራሻ
    - የአድራሻ መስመር 1
    - የአድራሻ መስመር 2
    - ከተማ
    - ዚፕ ኮድ
    - ግዛት
    - ካውንቲ

- ዝርዝር: ስለ ድርጅትዎ የተመለከተ አጭር መግለጫ (ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ አገልግሎቶች፣ ትኩረት) ከ750 ሆሄያት ይግለጹ።

- የስራ ቦታ ስም: ለይተው ይግለጹ (ከድርጅት ጋር ተመሳሳይ መምረጫ አማራጭ)
  ማስታወሻ: የተለያዩ አይነት የስራ ቦታዎች ወክለው የሚያመለክቱ ከሆነ እባክዎ ከእነዚህ የስራ ቦታዎች መካከል የአንዱን ስምና አድራሻ ብቻ ያካቱ።

- የስራ ቦታ አድራሻ: (ከድርጅት ጋር ተመሳሳይ መምረጫ አማራጭ)
    - የአድራሻ መስመር 1
    - የአድራሻ መስመር 2
    - ከተማ
    - ዚፕ ኮድ
    - ግዛት
    - ካውንቲ

- የፕሮግራም ስም: (ከድርጅት ጋር ተመሳሳይ መምረጫ አማራጭ)
  ማስታወሻ: ማስታወሻ: የሚያመለክቱት ከአንድ በላይ ለሆኑ ፕሮግራሞች ከሆነ፣ እባክዎ ከእነዚህ ፕሮግራሞች መካከል የአንዱን ስምና ዝርዝር ብቻ ያስገቡ።

- ዝርዝር: ስለፕሮግራሙ የተመለከተ አጭር ዝርዝር (ማን እንደሆነ፣ የፕሮግራም ትኩረት) ከ750 ቃላላት ባልበለጠ ያቅርቡ።

- እዚህ ላይ ሪፖርት የሚደረጉ አመልካች ድርጅት፣ እና የስራ ቦታዎችና ፕሮግራሞች ስሞች እና የስራ ቦታዎች በኢሊቬት ዋሽንግተን/ Elevate Washington የህዝብ የወጣቶች ፕሮግራም ማውጫ ላይ ይካተታሉ። የስራ ቦታው መገኛ ሚስጥር ከሆነ እባክዎ ቦታው በፕሮግራሙ ማውጫ ላይ እንዳይካተት ለማድረግ እዚህ ጋር ምልክት ያድርጉ።

## የብቁነት መረጃ

እባክዎ ተግባራዊ በሚሆኑት ሳጥኖች ላይ ምልክት ያድርጉ:

- ☐ በ501 (c)(3) ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይም በ 501 (c)(3) በገንዘብ ስፖንሰር የሚደረግ ድርጅት
- ☐ ፕሮግራሜ/ድርጅቴ ከCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት በፊት ለህጻናት እና እድሜያቸው ከ5-24 አመት ለሆኑ ወጣቶች የወጣቶች ልማት አገልግሎቶችን ያቀርብ ነበር።
- ☐ ከመጋቢት እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ድረስ ፕሮግራሜ/ድርጅቴ ለወጣቶች በአካል፣ በቨርቹዋል ወይም በቀጥተኛ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ድጋፍ አማካኝነት ያቀርባል እና/ወይም ለማቅረብ አቅዷል።
- ☐ ፕሮግራሜ/ድርጅቴ በ COVID-19 ወረርሽኝ የተነሳ ኔጋቲቭ/አሉታዊ የገንዘብ ተጽእኖ አጋጥሞታል።

ፕሮግራሜ/ድርጅቴ ከ COVID-19 ወረርሽኝ መከሰት በፊት የሚከተሉትን አገልግሎቶች ያቀርብ ነበር፡

- ☐ ከትምህርት ሰዐት በኋላና የበጋ ፕሮግራሞች የመሳሰሉ የትምህርት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት
- ☐ ክትትል
- ☐ በትምህርት ቤት መቼት ውስጥ የተቀናጁ ከወጣቶች ማህበራዊ/ስነ ልቡና እና የትምህርት ያልሆኑ ድጋፎች ጋር የተገናኙ ጥቅል አገልግሎቶች።

ፕሮግራሜ/ድርጅቴ ከ COVID-19 ወረርሽኝ መከሰት በፊት በሚከተሉት የእድሜ ደረጃዎች ለሚገኙ ህጻናት እና ወጣቶች የወጣቶች ልማት አገልግሎቶችን ያቀርብ ነበር፡

- ☐ 5-12
- ☐ 13-18
- ☐ 19-24

## ቅድሚያ የሚሰጣቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን እና የCOVID-19 ተጽእኖን የተመለከተ መረጃ

እባክዎ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚሰጧቸው መልሶች ተግባራዊ የሚሆኑት እርስዎ የገንዘብ ድጋፍ ለሚጠይቁበት የወጣቶች ልማት ፕሮግራም ወይም የወጣቶች ልማት ድርጅት ላይ ብቻ መሆኑን ያረጋግጡ። ለምሳሌ የሚያመለክቱት በትልቅ ደረጃ ለሚሰራ፣ የተለያዩ አገልግሎቶች ለሚያቀርብ ድርጅት ከሆነ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጧው መልሶች በዚህ የወጣቶች ልማት ፕሮግራም ላይ ብቻ ተግባራዊ መሆን አለባቸው።

1. **ቅድሚያ በሚሰጣቸው ማህበረሰብ ውስጥ አገልግሎት ያገኙ ወጣቶች።** የድጋፍ ፈንድ ኢንቨስትመንቶች ከትምህርት ፍትህ ለራቁ ወጣቶች ቅድሚያ ይሰጣሉ።

   a. እባክዎ የወጣቶች ልማት ፕሮግራምዎ/ድርጅትዎ ትኩረት የሆኑ ቅድሚያ የሚሰጧቸው ወጣት የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ምልክት ያድርጉ፡

      - ☐ ለነጻ ወይም በቅናሽ ዋጋ በሚቀርብ ምሳ በሚለካው መሰረት በድህነት ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች
      - ☐ BIPOC ወጣቶች
      - ☐ ስደተኛ ወጣቶች
      - ☐ ስደተኛ እና/ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ወጣቶች
      - ☐ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች
      - ☐ መኖሪያ ቤት አልባ ወጣቶች
      - ☐ በአሳዳጊ እንክብካቤ ስር ያሉ ወጣቶች
      - ☐ LGBTQ ወጣቶች
      - ☐ በወንጀል ፍትህ ስርአት ስር ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶች

- ▫ አካል ጉዳተኛ ወጣቶች አካላዊ፣ የእድገት፣ እና/ወይም የንቃተ ህሊና አካል ጉዳቶች፣ ወይም ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያሏቸው ወጣቶችን ጨምሮ
- ▫ ፕሮግራሜ/ድርጅቴ በየትኛውም ከላይ የተጠቀሱት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ወጣት የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት አያደርግም

b. ፕሮግራምዎ አገልግሎት የሚሰ
መካከል በፕሮግራምዎ ላይ ተሳታፊ የሆኑት ላይ ምልክት ያድርጉ፡

- ▫ የአሜሪካ ህንዳውያን/የአላስካ ተወላጆች
- ▫ እሲያውያን/እሲያዊ አሜሪካውያን
- ▫ ጥቁር/አፍሪካ አሜሪካውያን
- ▫ የሂስፓኒክ ወይም ላቲኖ የዘር ሀረግ ያላቸው
- ▫ መካከለኛው ምስራቅ ወይም ሰሜን አፍሪካውያን
- ▫ የተለያየ የዘር ሀረግ ያላቸው
- ▫ የሀዋይ ተወላጆች/የፓሲፊክ አይላንደር

c. እባክዎ ባመለከቷቸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ስር ተካተው በዋናነት በፕሮግራምዎ/ድርጅትዎ ስር አገልግሎት የሚያገኙ ወጣቶችን መቶኛ ግምት ይስጡ: _____________

d. በፕሮግራምዎ/ድርጅትዎ ውስጥ ስለሚሳተፉ ወጣቶች ማወቅ እንፈልጋለን። የፕሮግራምዎ/ድርጅትዎ ወጣቶች ከላይ በተጠቀሱት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ወጣት የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ እንዴት እንደሚወከሉ ይግለጹ። የወጣት የማህበረሰብ ክፍሎች ብዛትዎ ላይ በ COVID-19 የተነሳ ለውጥ ከተፈጠረ ለምን እንደተፈጠረ በግልጽ ያብራሩ። እባክዎ ምላሽዎን በ 2,600 ፊደሎች ይገድቡ። የዚህ ጥያቄ መልስ የጠቅላላ ውጤቱን 50% ድርሻ ይይዛል።

2. **የፕሮግራሞች/ድርጅቶች ሰራተኞችና አመራር።** የድጋፍ ፈንድ ኢንቨስትመንቶች ቅድሚያ በሚሰጧቸው ወጣት የህብረተሰብ ክፍሎች ለሚገለጹ ፕሮግራሞች/ድርጅቶች ቅድሚያ ይሰጣሉ።

   a. ሰራተኞችዎ፣ አመራርዎ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድዎ እና በጎ ፍቃደኞችዎ እንዴት ቅድሚያ የሚሰጧቸው ወጣት የማህበረሰብ ክፍሎችን እንደሚገልጹ ያብራሩ። እባክዎ ምላሽዎን በ 2,200 ፊደሎች ይገድቡ። የዚህ ጥያቄ መልስ የጠቅላላ ውጤቱን 20% ድርሻ ይይዛል።

3. **የ COVID-19 ወረርሽኝ የፈጠረው ተጽዕኖ።** የድጋፍ ፈንዱ የተዘጋጀው የ COVID-19 ወረርሽኝ በመላው ዋሽንግተን በወጣቶች ልማት ፕሮግራሞች/ድርጅቶች ላይ የፈጠራቸውን አንዳንድ ተጽኖዎችን ለመቅረፍ ታስቦ ነው።

   a. እባክዎ የ2019 ዓ.ም እና (የታቀደ) የ2020 ዓ.ም የተጠቃለለ የፋይናንስ መረጃ ያቅርቡ:

   - የ2019 ዓ.ም የወጣቶች ልማት ፕሮግራም/ድርጅት ገቢ: $_____
   - የ2019 ዓ.ም የወጣቶች ልማት ፕሮግራም/ድርጅት ወጪ: $_____

- (የታቀደ) የ2020 ዓ.ም የወጣቶች ልማት ፕሮግራም/ድርጅት ገቢ: $_____

- (የታቀደ) የ2020 ዓ.ም የወጣቶች ልማት ፕሮግራም/ድርጅት ወጪ: $_____

ለ. እባክዎ እንዴት የወጣቶች ልማት ፕሮግራምዎ/ድርጅትዎ እንዴት በCOVID-19 የተነሳ የገንዘብ ተጽእኖ እንደተፈጠረበት ያብራሩ። በሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች ላይ የፈጠራቸው ተጽእኖዎች ምንድን ናቸው? የCOVID-19 ወረርሽኝ በገቢዎ ላይ ተጽእኖ የፈጠረው እንዴት ነው? የCOVID-19 ወረርሽኝ በወጪዎችዎ ላይ ተጽእኖ የፈጠረው እንዴት ነው? የፔይሮል ጥበቃ ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍን ጨምሮ ለፕሮግራምዎ/ድርጅትዎ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጉ የነበሩ የመንግስት ወይም የግል የ COVID-19 የገንዘብ ድጋፍ አድራጊዎች ይዘርዝሩ። እባክዎ ምላሽዎን እስከ 2,200 ፊደdሎች ይገድቡ። የዚህ ጥያቄ መልስ የጠቅላላ ውጤቱን 30% ድርሻ ይይዛል።

**ማረጋገጫዎች:**

ይህን ቅጽ የሞላው ሰው ስም:

የኢሜይል አድራሻ: ስልክ ቁጥር:

ይህ የእርዳታ ገንዘብ የሚሰጣቸው ሁሉም አመልካቾች ተሞልቶ የተፈረመ W-9 ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። የእርዳታ ክፍያዎቹ በ Automated Clearing House (ACH) አማካኝነት በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ይከፈላሉ። ስኩልስ አውት ዋሽንግተን/ School's Out Washington ለእርዳታ ፈንዱ ተመራጮች በDocuSign አማካኝነት የACH ፍቃድ መስጫ ቅጽ እና W-9 ቅጽ ይልካል። እነዚህን ሰነዶች በተሰጡ በሰባት ቀናት ውስጥ መልሶ መላክ ያስፈልጋል። እባክዎ የ ACH ቅጹ እና የW-9 መጠየቂያ ለማን መላክ እንዳለባቸው ይግለጹ:

ስም: የኢሜይል አድራሻ:

አንድ አመልካች የድጋፍ እርዳታው ከተሰጠው እርዳታው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት አመታት ውስጥ ለስኩል አውት ዋሽንግተን/ School's Out Washington የአመልካቹን ቅጽ 990 እና ሌሎች የፋይናንስ መዝገቦች በዚህ ማመልከቻ ላይ የቀረበውን የፋይናንስ መረጃ ለማረጋገጥ በሁሉም አሳማኝ ጊዜያት የማግኘት መብት ለመስጠት ይስማማል።

"የአመልካቹን ድርጅት ወክዬ ይህን ማመልከቻ ለማቅረብ ፍቃድ የተሰጠኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ።"

"ይህን ማመልከቻ በመፈረም አመልካቹ ድርጅትም ሆነ ወካዮቹ በአሁኑ ወቅት በየትኛውም የፌደራል መምሪያ ወይም ድርጅት በዚህ ግብይት ላይ እንዳይሳተፉ ያልታገደዱ፣ ያልተከለከሉ፣ ለእገዳ ያልቀረቡ፣ ብቁ ያለመሆን መግለጫ ያልወጣባቸው ወይም በፍቃደኝነት ያልተገለሉ መሆኑን አረጋግጣለሁ።"

"በዚህ ማመልከቻ ላይ የቀረበው መረጃ እና በየትኛውም ደጋፊ ሰነዶችና ቅጾች ላይ የቀረበው መረጃ በሁሉም የፍሬ ነገር ይዘቶች እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ከዚህ በተጨማሪም የትኛውንም ሀሰተኛ መግለጫዎች መስጠት ወይም ሆን ብሎ ከዚህ ማመልከቻ ላይ መረጃ ማጉደል የእርዳታ ገንዘቡን የመመለስ ወይም ለማጭበርበር ድርጊቱ ሌሎች የህግ እርምጃዎችን እንደሚያስከትልብኝ ተረድቻለሁ።"

**ይህ ፕሮጀክት ከአሜሪካ የግምጃ ቤት መምሪያ በተሰጠ የገንዘብ ድጋፍ የተደገፈ ነው። በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረቡት የእይታ ነጥቦች የጸሃፊው እይታዎች ሲሆኑ፣ የአሜሪካን የግምጃ ቤት መምሪያ ኦፊሴላዊ አቋም ወይም ፖሊሲዎችን የግድ አይወክሉም። እነዚህ የገንዘብ ድጋፎች የሚተዳደሩት በዋሽንግተን ስቴት የንግድ መምሪያ የአነስተኛ ንግድ የመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ፕሮግራም ነው።**